# “ብቁ ወጣት”

## ሺህ ሆነን እንደ አንድ አንድ ሆነን እንደ ሺህ

ወጣቱን ለፅናት፣ ለተሻለ ሙያዊ ክህሎት እና ለብሩህ ዘመን ለማብቃት ሁሉን አቀፍ ርብርብ የሚጠይቅ ስለሆነ ሁሉም ባለ ድርሻ በመሆን የበኩሉን ሊወጣ ይገባል፡፡

ሃገር እንደ ሃገር እንድትቀጥል የተማሩ፣ ብቁና አምራች ወጣት ዜጎች ያስፈልጓታል፡፡ ወጣትነት ትኩስ ጉልበትን ከብሩህ አዕምሮ ጋር በማጣመር ለለውጥ መዘጋጀትን ወይም ለውጥ ፈላጊነትን አጉልቶ የሚያሳይ ነውና፡፡

ይህን ሰናይ አላማ ለማሳካት ይመስላል የአማራ ልማት ማህበር ከማስተር ካርድ ፋውንዴሽን እና ከዩኒሴፍ ጋር በመተባበር ግጭት በነበረባቸው ወረዳዎች ወጣቶችን ለመደገፍና ለማብቃት የ“ብቁ ወጣት” ፕሮግራም በማዘጋጀት እየሰራ ይገኛል፡፡

ማስተር ካርድ ፋውንዴሽን መቀመጫውን ካናዳ ያደረገ ግብረ ሰናይ ድረጅት ነው፡፡ የአማራ ልማት ማህበር (አልማ) ደግሞ ከዩኒሴፍና ከማስተር ካርድ ፋውንዴሽን የሚገኘውን ገንዘብ ለተጠቃሚዎቹ በማድረስ በኩል በበላይነት ይመራዋል፡፡ ይህ ፕሮግራም በኢትዮጵያ ማለትም በጦርነት ምክንያት ጉዳት በደረሰባቸው አማራ፣ ትግራይና አፋር ክልሎች ላይ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡ በግጭቱ ተጎጂ ናቸው ተብለው በሚገመቱ የህብረተሰብ ክፍሎች በተለይም ወጣት ሴቶችና ወንዶች እንዲሁም አካል ጉዳተኞች ላይ ትኩረት ይሰጣል፡፡

እንደ ሃገር በ50 ወረዳዎች ላይ ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን እድሜያቸው ከ15-29 ድረስ ያሉ ወጣቶችን በማካተት በሶስት ዓመታት ውስጥ ከ120 ሺህ በላይ ወጣቶችን ለማብቃት እየሰራ ይገኛል፡፡ እንደ አማራ ክልል ደግሞ ከ68 ሺ በላይ ወጣቶችን ተጠቀሚ የሚያደርግ ነው፡፡ በተጨማሪም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችንና የሙያ ቴክኒክ ተቋማትን ለወጣቶች ምቹ በማድረግ ሰፊ እድሎችን ለመፍጠር ጥረት እያደረገ ያለ ፕሮግራም ነው፡፡

የ“ብቁ ወጣት” ፕሮግራም በሶስት ዋና ዋና ነጥቦች ላይ ትኩረት ሰጥቶ የሚሰራ ፕሮግራም ነው፡፡ እነዚህም ወጣቶችን ለስራ ዝግጁ ማድረግ፣ በትምህርትና በስልጠና ማገዝ እና ከትምህርት ውጭ የሆኑና በትምህርት ላይ ያሉትን በይቻላል መንፈስ ወደ ስራ በማስገባት የእውቀት እና የክህሎት ሽግግር በማድረግ በስራ እንቅስቃሴያቸው ውጤታማ እንዲሆኑ

ማስቻል ነው፡፡ በሌላ መልኩ የስራ ዕድል መፈጠሩ በራሱ ደግሞ ወጣቶች ያላቸውን ጸጋ አውጥተው እንዲጠቀሙ የሚያስችል አቅም ይፈጥርላቸዋል፡፡

ይህ ፕሮግራም አላማው በግጭት ውስጥ የነበሩ ወጣቶችን ከገቡበት ድባቴ በማውጣት በትምህርት፣ በጤናና በኑሮ ሁኔታቸው የተሻሻሉ ለማድረግ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ያለ ክህሎት እና እውቀት ወደ ስራ የሚገቡ  ወጣቶችን በዕውቀትና ክህሎት የተደገፉ የሙያ ባለቤት ከማድረግ ባሻገር  በፋይናንስና በቴክኒክ እውቀት በመደገፍ የገበያ ትስስርን በመፍጠር የኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ከፍ ለማድረግ ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡

በዚህ መሰርትም 80 በመቶ ለሴቶች 10 በመቶ ደግሞ ለአካል ጉዳተኞች ኢንዲሁም ቀሪው 10 በመቶ ደግሞ ለወጣቶች ቅድሚያ ይሰጣል፡፡ ይህ ፕሮግራም በአማራ ክልል ተግባራዊ ሲደርግም በተመረጡ 23 ወረዳዎች በአመት ከ23 ሺ በላይ ወጣቶችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው፡፡

ይህ ፕሮግራም የጋራ ርብርበን የሚጠይቅ ሲሆን የወጣቶችን የስራ ፈጠራ በማሳደግና በማበረታታት ለሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ሞዴል በማድረግ ተነሳሽነት ለመፍጠር ያስችላል፡፡

የ"ብቁ ወጣት" ፕሮግራም በርካታ ባለ ድርሻ አካላትን የሚያሳትፍ ፕሮግራም ነው፡፡ ለአብነትም ገንዘብና ኢኮኖሚ ቢሮ በፋይናንስ ዘርፍ ያለውን ስራ አብሮ የሚያግዝ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የክልሉ ትምህርት ቢሮ፣ ፍትህ ቢሮ፣ ስራና ስልጠና ቢሮ እና የመሳሰሉት በየ ደረጃው ይሳተፋሉ፡፡

በዚህ ረገድ ለወጣቶች የመማርና የመበልጸግ እድልን በመፍጠር በአፍሪካ እስከ 2030 ዓ.ም ከ10 ሚሊዮን በላይ ወጣቶችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ይሆናል፡፡

ስለሆነም እንደዚህ አይነት ፕሮግራሞች መጀመራቸው ለወጣቱ ማህበረሰብ ትልቅ መነሳሳትን የሚፈጥር ከመሆኑም ባሻገር በሃገራዊ ስሜት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ በቀጣይም ከሃገሪቱ ሁሉን አቀፍ እድገት ላይ የራሳቸውን አሻራ በማሳረፍ እንዲሁም የሃገር ፍቅር ስሜታቸው እንዲጨምር ስለሚያደርግ በፖለቲካዊ፣ ማበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፉ ላይ ከፍተኛ መነቃቃትን የሚፈጥርና  የመወሰን ስሜት እዲኖራቸው ስለሚያስችል ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡